# የግል መረጃ አጠቃቀም ማስታወቂያ

***ይህ ማስታወቂያ የእርስዎ የህክምና መረጃዎች እንዴት ጥቅም ላይ ሊውሉ እና ሊገለጹ እንደሚችሉ፣ እንዲሁም እነዚህን መረጃዎች እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ያብራራል።***

**እባክዎን በጥንቃቄ ይመልከቱት።**

በሜሪስ የእናቶች እና ህፃናት እንክብካቤ ማእከል (“Mary’s Center”)፣ ስለእርስዎ የተጠበቀ የጤና መረጃ (Protected Health Information) በኃላፊነት ስሜት ለመጠቀም እና ለማስተናገድ ተግተን እየሠራን ነው። ጥብቅ የግል የጤና መረጃዎን እንድንጠብቅ፣ ከጤና መረጃዎ ጋር በተያያዘ ስላለን ሕጋዊ ግዴታዎች እና የግል መረጃ አጠቃቀምን ለእርስዎ እንድናሳውቅ፣ እንዲሁም ጥበቃ ያልተደረገለት የጤና መረጃ ደህንነት ከተጣሰ የተጎዱ ግለሰቦችን እንድናሳውቅ በሕግ ይጠበቅብናል። ይህ ማስታወቂያ ከመረጃዎ ጋር በተያያዘ ያሉንን ግዴታዎች እና የእርስዎን መብቶች ያጠቃልላል። ይህ ማስታወቂያ በፌደራል ደንቦች በተደነገገው መሠረት በሁሉም የተጠበቀ የጤና መረጃ ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

1. ***ያለእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ መጠቀም እና መግለጽ የሚንችላቸው።***

የእርስዎን የጽሁፍ ፈቃድ ሳይያስፈልገን የጤና መረጃዎን ለተወሰኑ ዓላማዎች ልንጠቀምበት ወይም ልንገልጸው እንችላለን፣ ከእነሱም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

**ህክምና፡** መረጃዎን እርስዎን ለማከም ዓላማ ልንጠቀምበት ወይም ልንገልጸው እንችላለን። ለምሳሌ፣ ህክምና እንዲሰጡዎት መረጃዎን ለሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ልንገልጽ እንችላለን፤ የቀጠሮ ማስታወሻዎችን ልንልክ እንችላለን፤ ወይም ስለምንሰጣቸው የህክምና አማራጮች ወይም አገልግሎቶች መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።

**ክፍያ፡** ኀተደረገሎት አገልግሎቶች ክፍያ ለማግኘት መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም ልንገልጸው እንችላለን። ለምሳሌ፣ ለህክምናው ክፍያ ለማግኘት መረጃውን ለጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎ ወይም ለሌላ ክፍያ ፈጻሚ አካል ልንገልጽ እንችላለን።

**የጤና እንክብካቤ ስራዎች፡** ተቋማችንን ለማንቀሳቀስ እና ታካሚዎቻችን ጥራት ያለው እንክብካቤ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ለሆኑ የተወሰኑ እንቅስቃሴዎች መረጃዎን ልንጠቀምበት ወይም ልንገልጸው እንችላለን። ለምሳሌ፣ የሰራተኞቻችንን ብቃት ለማሰልጠን ወይም ለመገምገም ወይም በተቋሙ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ መረጃን ልንጠቀም እንችላለን።

**ሌሎች አጠቃቀሞች ወይም መግለጫዎች፡** በተጨማሪም በ45 CFR § 164.512 ወይም በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች እና ደንቦች በተፈቀደው መሠረት መረጃዎን ለሌሎች የተወሰኑ ዓላማዎች ልንጠቀምበት ወይም ልንገልጸው እንችላለን፣ ከእነሱም መካከል፡-

- በጤናዎ ወይም በደህንነትዎ፣ ወይም በሌሎች ሰዎች ጤና ወይም ደህንነት ላይ የሚደርሰው ስጋትን ለማስወገድ።
- በደል፣ ተገቢ ትኩረት አለመስጠት ወይም ሌሎች የተወሰኑ ሁነቶችን ማሳወቅ የመሰሉ በስቴት ወይም በፌደራል ሕግ በሚጠየቀው መሠረት ።
- በሰራተኞች ካሳ ሂደቶች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል በሰራተኞች ካሳ ሕጎች በተፈቀደው መሠረት።
- ለተወሰኑ የሕዝብ ጤና ተግባራት ለምሳሌ፥ አንዳንድ በሽታዎችን ሪፖርት ማድረግ።
- ኦዲት፣ ምርመራ ወይም የፈቃድ እርምጃዎች ላሉ የተወሰኑ የሕዝብ ጤና ክትትል ተግባራት።
- በፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ ማዘዣ ወይም መጥሪያ በፍትህ ወይም አስተዳደራዊ ሂደቶች ላይ ምላሽ ለመስጠት
- እንደ ወታደራዊ ወይም ማረሚያ ተቋማት ላሉ ለተወሰኑ ልዩ የመንግስት ተግባራት።
- አንዳንድ ሁኔታዎች ከተሟሉ ለምርምር ዓላማዎች።
- የሕግ አስከባሪ አካላት የተሸሰኘን፥ ተጎጂ ወይም ምስክር ለማግኘት ወይም ሞትን ወይም የተወሰኑ ወንጀሎችን ሪፖርት ለማድረግ ለቀረቡት የተወሰኑ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት።

- የሬሳ መርማሪዎች (coroners)፣ የቀብር ዳይሬክተሮች ወይም የአካል ክፍሎች ማሰባሰቢያ ድርጅቶች ተግባራቸውን እንዲወጡ ለማስቻል።

**2. እርስዎ ካልተቃወሙ በስተቀር ልንገልጻቸው የምንችላቸው ነገሮች፡** አሰራሩ ሌላ እንዲሆን ካላዘዙን በስተቀር፣ ከዚህ በታች በተገለፀው መሠረት መረጃዎን ልንገልጽ እንችላለን፦

- በጤና እንክብካቤዎ ወይም ለጤና እንክብካቤዎ በሚደረግ ክፍያ ውስጥ ለሚሳተፉ የቤተሰብዎ አባል፣ ዘመድ፣ ወዳጅ ወይም ሌላ ሰው። የዚያ ሰው ተሳትፎ ጋር አግባብነት ያለውን የመረጃ መግለጫ እንገድበዋለን።
- ከሌሎች HIE ጋር በመሆን የኮሎምቢያ ዲስትሪክትን የሚያገለግለውን CRISP DC የተባለውን ክልላዊ የጤና መረጃ ልውውጥ (“HIE”) ለመቀላቀል መርጠናል። CRISP DC በተጨማሪም ከአላስካ፣ ኮኔክቲከት፣ ሜሪላንድ እና ዌስት ቨርጂኒያ ከሚገኙት ጨምሮ ከሌሎች HIEዎች ጋር የተያያዘ እና መረጃ የሚጋራ ነው። በሕግ በተፈቀደው መሠረት፣ ፈጣን መዳረሻን፣ የተሻለ የእንክብካቤ ቅንጅትን ለማቅረብ እና ህክምና ሰጪዎች እና የሕዝብ ጤና ባለስልጣናት የተሻለ መረጃ ያላቸው ውሳኔዎችን እንዲያስተላልፉ ለመርዳት የጤና መረጃዎ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ከዚህ ልውውጥ ጋር ይጋራል። በ1-877-952-7477 በመደወል ወይም Opt-Out ፎርም ሞልተው በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በድረ-ገፃቸው www.crispdc.org በኩል ለCRISP DC በማስገባት በCRISP DC በኩል የሚገኘውን የጤና መረጃዎን መዳረሻ ማገድ (opt-out ማድረግ) ይችላሉ። እንደ የሕዝብ ጤና ሪፖርት ማድረግ እና የቁጥጥር የሚደረግባቸው አደገኛ ዕጾች (Controlled Dangerous Substances) መረጃ ያሉ በሕግ የሚጠየቁ የተወሰኑ ሪፖርቶች እርስዎ opt-out ቢያደርጉም እንኳ ለህክምና ሰጪዎች ክፍት ሆነው ይቆያሉ።

**3. በእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ መጠቀም እና መግለጽ የምንችላቸው፡** በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ያልተገለጹ ሌሎች አጠቃቀም እና መግለጽ የሚፈፀሙት የእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ሲኖር ብቻ ነው፤ ይህም አብዛኛዎቹን የስነ-ልቦና ህክምና ማስታወሻዎች አጠቃቀም ወይም መግለጽን እና ለአብዛኛዎቹ የማርኬቲንግ ዓላማዎች የሚደረጉትን ያካትታል። ከዚህ በታች ለተጠቀሰው የግላዊነት ተወካይ የጽሁፍ ማስታወቂያ በማስገባት ፈቃድዎን መሰረዝ ይችላሉ። መሰረዙ እኛ በፈቃዱ ላይ ተመስርተን እርምጃ በወሰድንበት መጠን ተፃሚ አይሆንም፦

- በህክምና ተቋማችን የአደንዛዥ ዕጽ ወይም የሱሰኝነት ህክምና እየተከታተሉ ከሆነ፣ ይህንን መረጃ በተለየ ሁኔታ ለማጋራት ስምምነት ካልሰጡ በስተቀር መረጃዎ በCRISP DC በኩል አይጋራም። ለመስማማት ከመረጡ፣ የሱሰኝነት ህክምና መረጃዎ እርስዎን ከሚያክሙ ሌሎች ክሊኒኮች ጋር፣ ለአገልግሎት ክፍያ እና እንደ ጥራት ማሻሻል እና የእንክብካቤ ቅንጅት ላሉ ሌሎች የስራ እንቅስቃሴዎች ይጋራል። በአሁኑ ጊዜ መረጃዎን ለማጋራት፣ ስምምነትዎ ከህክምና፣ ክፍያ እና ስራዎች ጋር ለተያያዙ ዓላማዎች በሙሉ መረጃዎን ማጋራትን የሚፈቅድ መሆን አለበት። እንዴት ስምምነት መስጠት እንደሚችሉ፣ ስምምነቱ ምን ማለት እንደሆነ እና ስምምነትዎን እንዴት መሰረዝ እንደሚችሉ ለበለጠ መረጃ ክሊኒክዎን መጠየቅ ይችላሉ።

**4. ጥብቅ የጤና መረጃዎን በተመለከተ ያሉቆት መብቶች፡** ከጤና መረጃዎ ጋር በተያያዘ የሚከተሉት መብቶች አሉዎት። ከእነዚህ መብቶች ውስጥ ማንኛውንም ለመጠቀም፣ ከዚህ በታች ለተጠቀሰው የግል መረጃ ኦፊሰር የጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ አለብዎት፦

- ለህክምና፣ ክፍያ ወይም የጤና እንክብካቤ ስራዎች የመረጃ አጠቃቀም ወይም መግለጫ ላይ ተጨማሪ ገደቦች እንዲደረጉ መጠየቅ ይችላሉ። እርስዎ ወይም ሌላ ሰው ስለ አንድ እቃ ወይም አገልግሎት ክፍያ ከከፈሉ እና ስለዚያ እቃ ወይም አገልግሎት የሚገልፅ መረጃ ለጤና ኢንሹራንስ ሰጪ እንዳይገለፅ ከጠየቁበት ከተወሰነ ሁኔታ በስተቀር የተጠየቀውን ገደብ ለመቀበል አንገደድም።
- በተለምዶ በስልክ፣ በመኖሪያ አድራሻዎ በፖስታ፣ እና የኢሜይል አድራሻዎን የሰጡ ከሆነ በኢሜይል እንገናኝዎታለን። በሌሎች አማራጭ መንገዶች ወይም በሌሎች ቦታዎች እንድንገናኝዎት መጠየቅ ይችላሉ። ምክንያታዊ ጥያቄዎችን እንቀበላለን።
- ስለ እንክብካቤዎ ወይም ስለ እንክብካቤዎ ክፍያ ውሳኔ ለመስጠት የሚያገለግሉ መዝገቦችን፣ የኤሌክትሮኒክስ ኮፒ ጨምሮ፣ መመርመር እና ግልባጭ ማግኘት ይችላሉ። መዝገቦቹን ለማቅረብ ምክንያታዊ የሆነ የወጪ መሸፈኛ

ክፍያ ልናስከፍልዎ እንችላለን። በተወሰኑ ሁኔታዎች ጥያቄዎን ልንከለክል እንችላለን፤ ለምሳሌ መረጃውን መግለጽ በእርስዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ያሰድሳል ብለን ካመንን።

- ጥብቅ የጤና መረጃዎ እንዲስተካከል መጠየቅ ይችላሉ። በተወሰኑ ምክንያቶች ጥያቄዎን ላንቀበል እንችላለን፤ ለምሳሌ መዝገቡን መጀመሪያውኑ እኛ ካልከፈትነው ወይም መዝገቡ ትክክለኛ እና ሙሉ መሆኑን ካመንን።
- በትብቅ የጤና መረጃዎ ላይ ያደረግናቸውን የተወሰኑ የመረጃ መግለጫዎች ዝርዝር (accounting of disclosures) ማግኘት ይችላሉ። የመጀመሪያውን ዝርዝር መረጃ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያለምንም ክፍያ ማግኘት ይችላሉ። ከዚያ በኋላ በዚያው የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለሚቀርቡ ማናቸውም ተጨማሪ ጥያቄዎች፣ በተገቢው ወጪ ላይ የተመሰረተ ክፍያ ልናስከፍል እንችላለን።
- ከጠየቁ የዚህን ማስታወቂያ የወረቀት ግልባጭ ማግኘት ይችላሉ። ማስታወቂያውን በኤሌክትሮኒክስ ኮፒ ለመቀበል ተስማምተው ቢሆንም እንኳ ይህ መብት አለዎት።

**5. በዚህ ማስታወቂያ ላይ ተደረጉ ለውጦች:** በማንኛውንም ጊዜ የዚህን ማስታወቂያ ውሎች የመቀየር፣ እና አዲሱን ማስታወቂያ እኛ በምንይዘው በሁሉም ጥብቅ የጤና መረጃ ላይ ተግባራዊ የማድረግ መብታችን የተጠበቀ ነው። የግል መረጃ አጠቃቀም ላይ ጉልህ ለውጥ ካደረግን፣ የአሁኑን ማስታወቂያ ቅጂ/ግልባጭ መቀበያ ቦታችን እና በድረ-ገጻችን ላይ እናሳውቃለን። የማስታወቂያውን ግልባጭ ከእንግዳ መቀበያ ዴስካችን ወይም ከግል መረጃ ጉዳዮች ኦፍሰራችን ማግኘት ይችላሉ።

**6. ቅሬታዎች:** የግል መረጃ መብቶችዎ ተጥሰዋል ብለው ካመኑ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። እባክዎን ቅሬታዎን ለግል መረጃ ጉዳዮች በማሳወቅ ወይም ለስፒክ-አፕ እና ሪፖርት መስመራችን (Speak-UP & Report Line) ላይ ሪፖረት በማድረግ (ስልክ፡ 844.237.8634 ወይም በድረ-ገጽ፡ maryscenter.ethicspoint.com) ቅሬታዎን ያቅርቡ። ሁሉም ቅሬታዎች በጽሁፍ መሆን አለባቸው። ቅሬታ በማቅረብዎ ምክንያት ምንም ዓይነት የበቀል እርምጃ አንወስድም።

**7. የምገኙበት አድራሻ መረጃ:** ስለዚሁ ማስታወቂያ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ ወይም ለማንኛውም የመረጃ አጠቃቀም ወይም መግለጫ መቃወም ወይም ቅሬታ ማቅረብ ከፈለጉ ወይም ከላይ የተብራሩትን ማንኛውንም መብት ለመጠቀም ከፈለጉ፣ እባክዎን በሚከተለውን ያግኙ፦
Mary’s Center
Attn: VP of Compliance
2333 Ontario Road, NW
Washington, DC 20009
Email: privacy@maryscenter.org

**8. ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን፦** ይህ ማስታወቂያ ከኦክቶበር 2፣ 2024 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።